# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ)
# *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(አንድነት/United)

ነሃሴ ፰ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ. ም
August 14, 2016

## ሕዝባዊ ትግል በድል መጠናቀቁ አይቀሬ ነው!

በደልና መከራ የበዛበት ሕዝብ ጨቋኝ አገዛዝን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከትክሻው ላይ አሽቀንጥሮ ለመጣል ክንዱን አጠንክሮ መነሳቱ አይቀሬ መሆኑ ታሪካዊ ሃቅ ነው። ትዕግሥቱ የተሟጠጠበት ሕዝብ አንድ ጊዜ ቆርጦ ከተነሳ ደግሞ የአምባገነን አፈና፣ ፉከራና ድንፋታ ከቶውንም ሊመልሰው እንደማይችልም የታወቀ ነው። በአገራችን ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍቶ የነበረው የዘውድ አገዛዝ፣ ሕዝብ በፍርሃት ተውጦ ሰጥለጥ ብሎ እንዲገዛለት ሲያደርግ የነበረውን የተንኮል ሰንሰለት የኢትዮጵያ ሕዝብ በ1966 ዓ. ም በጣጥሶ በአንድነት ሆ! ብሎ ለተቃውሞ በመነሳቱ፣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ግብዓት መሬት ሊከተው መቻሉ አቢይ ታሪካዊ መረጃ ነው።

ኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት) በ1966 ዓ. ም በአገራችን የታየው ሁኔታ እነሆ ዛሬም ሊደገም እያኮበኮበ መሆኑን ያምናል፤ ይህን የሕዝብ እንቅስቃሴም ሙሉ በሙሉ ይደግፋል፤ ከሕዝቡ ጎንም ይቆማል። በኦሮምኛ ተናጋሪዎችና በተለያዩ አካባቢዎች ሲቀጣጠል የነበረው የሕዝብ አመፅ ሰሞኑን በጎንደርና በባህርዳር እንዲሁም በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እየተንቦገቦገ ነው። በኦሮምኛ ተናጋሪዎች አካባቢ ሲደረግ የቆየው ሕዝባዊ ተቃውሞ በበለጠ ተጠናክሮ ሥር-ነቀል በሆነ መንገድ የአምባገነኑን የብረት አጥር ፈንቅሎ በመውጣት እያሳየ ያለው ኢትዮጵያዊ ወኔ እጅግ የሚያኮራ ነው። በሌሎች አካባቢዎችም በአሁኑ ሰዓት በተግባር እየተወሰደ ያለው ተመሳሳይ እርምጃ አበረታች ነው። በአሁኑ ሰዓት የተቀጣጠለው የእሳት ወላፈን በህወሓት ድንፋታና የወታደር አፈና ፈጽሞ ሊበርድ የሚችል አይደለም። የእሳቱ እቶን በበለጠ ተቀጣጥሎ ትግሉን ፈጣን በሆነ መንገድ


**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

ህወሓት ወደ መሸገበት ቤተ-መንግሥት ያደርሰዋል እንጂ ከቶውንም ሊያዳፍነው አይችልም።

ትዕግሥተኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሃያ አምስት ዓመታት ዴሞክራሲያዊ መብታችን ይከበር እያለ በሰላማዊ መንገድ በጠየቀ ቁጥር፣ አምባገነናዊው የህወሓት አገዛዝ በብረት አለሎ ረግጦ ለዘላለም የሚገዛ መስሎት የሚችለውን የማፈኛ መሣሪያ ሁሉ በመጠቀም፣ የሕዝብን አመፅ ሊያዳፍን ሲሞክር ቆይቷል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በደሉ በዝቶበት ከሚችለው በላይ ስለሆነና ትዕግሥቱንም አሟጦ ስለጨረሰ፣ የአፈና ቀንበሩን አሽቀንጥሮ ጥሎና <u>የማዕቀብ</u> ክልሉን ፈንቅሎ በቆራጥነት ተምሞ ወጥቷል።

የህወሓት አገዛዝ <u>ሥልጣኑን የሥልጣን ምንጭ ለሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከማስረከብ ውጪ አማራጭ የለውም። በደልና ሰቆቃ አስመርሮት የተነሳን ሕዝብ አፍናለሁ ብሎ ማሰብ በገዛ አንገቱ ላይ ገመድ መጠምጠም መሆኑን ሊገነዘበው ይገባል እንላለን። በዚህ አጋጣሚ</u> እስካሁን ድረስ ከህወሓት ጋር አብራችሁ በሕዝብ ትከሻ ላይ ስትናጥጡ የነበራችሁ ግብረ-በላዎችም ከአሁኑ ሕዝብን ይቅርታ እየጠየቃችሁ ከሕዝብ ጋር እንድትወግኑና የበደላችሁትን ሕዝብ የትግል አጋሩ በመሆን ልትክሱት ይገባል እንላለን።

መለዮ-ለባሹም በታሪክና በሕግ የተደነገገልህን የአገር ዳር-ድንበርን ማስከበርና የሕዝብን ደህንነት የመጠበቅ ተግባርህን ማጠናከር ኃላፊነትህ መሆኑን ለማሳሰብ እንወዳለን። ፀረ-ሕዝብ ከሆነው ከህወሓት ጋር አብረህ በሕዝብ ላይ እጅህን አታንሳ! በታሪክ ተጠያቂ እንዳትሆን ያለህ አማራጭ ከሕዝብ ጋር መወገን ብቻ ነው። ወርሃዊ ደመወዝህን የሚከፍልህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግዴታህንና ኃላፊነትን በትክክል እንድትወጣ ይጠብቅብሃል። መንግሥታት ይለዋወጣሉ፤ የአገር መከላከያ ግን ከአገርና ከሕዝብ ጋር አብሮ የሚቀጥል የአገር አለኝታ ኃይል መሆኑን አትዘንጋ! ስለዚህ ታሪካዊ ተልዕኮህንና ተግባርህንም በሚገባ ለመወጣት ከሕዝብ ጎን እንድትሰለፍ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

አስተዋዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! በአስተዋይነትህ ህወሓትንና ሀገር ወዳዱን ሰፊውን የትግራይ ሕዝብ ለይተህ ትግልህን በህወሓትና በግብረ-በላዎች ላይ አነጣጥረህ

P.O.Box 91384 Phone: 202- 241 2078
Los Angeles, CA 90009 Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com

እንደቀጠልከው ሁሉ አሁንም ወደፊትም ለህወሓት እኩይና ከፋፋይ ሤራ ሰለባ ሳትሆን ትሁረትህን በትግል ዒላማህን ላይ አጠናክረህ ቀጥል። ኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት)ም ምን ጊዜም ከጎንህ እንደሚቆም ልናረጋግጥልህ እንወዳለን።

የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በኅብረትና በአንድነት እጅ ለእጅ ተያይዘን ይዋል ይደር ሳንል ከህወሓት ጋር ከሚዋደቀው ሕዝባችን ጎን ቆመን የመሪነት ኃላፊነታችንን መወጣት ካልቻልን፣ በታሪክ ተጠያቂ ከመሆን እንደማናመልጥ ተረድተን ግዳጃችንን እንድንወጣ ኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት) ጥሪውን ያቀርባል። የሕዝብ ማዕበል የህወሓትን አገዛዝ ጠራርጎ ከጣለ በኋላ ቀጣዩ ምን ሊሆን ይችላል? ምንስ መሆን ይገባዋል? ብለን መምከር ያለብን ጊዜ አሁን ነውና ሀገራችንን ለመታደግ በአንድነት እንታገል እንላለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
ሰፊው ሕዝብ ያቸንፋል!

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**